የሰበር መዝገብ ቁጥር 146727

ጥቅምት 20 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡- አቶ አክሊሉ አፈወርቅ ጠበቃ ናትናኤል ተክሉ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ነሐሴ 08 ቀን 2009 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሠሚ ችሎት በመ.ቁ 144037 ሐምሌ 28 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሠበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለቱ ነው፡፡ የአሁን አመልካችን ጨምሮ ሌሎች ሥድሥት ተከሳሾችን ክስ የተመለከተው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተጠሪን ማሥረጃዎች ከሰማ በኂላ ተከሳሾች በዋስ ሆነው ጉዳያቸውን እንዲከታተሉ ፈቅዷል፡፡ ተጠሪ በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረበው ይግባኝ መነሻነት ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤት ለአመልካች እና ለሥር ተከሳሾች የሰጠውን የዋስትና መብት በመሻር ጉዳያቸውን በማረሚያ ቤት ሆነው እንዲከታተሉ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 75/2 በዋስትና ጉዳይ ላይ ከአንድ ጊዜ በላይ ይግባኝ እንደማይኖር የተደነገገ በመሆኑ አመልካች አቤቱታውን ለሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ ከማሳረም ውጪ ሁለተኛ ይግባኝ ሊያቀርብ አይችልም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- አመልካች ከመነሻውም ቢሆን በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የዋስትና መብቴ ያልተከለከለ በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 75/2 ሁለተኛ ይግባኝ አይፈቅድም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካችን የዋስትና መብት የሻረው ተጠሪ ባቀረበው ይግባኝ መነሻነት ሆኖ ሳለ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በዋስትና ጉዳይ ላይ ሁለት ጊዜ ይግባኝ ማለት አይቻልም በማለት የአመልካችን የይግባኝ አቤቱታ ወድቅ ማድረጉ የሰጠው ውሳኔ ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 75/2 እና ከአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 9 አንጻር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ጥቅምት 02 ቀን 2010 ዓ/ም በሰጠው መልስ በሥር ፍ/ቤት የአመልካች የይግባኝ መብት መታለፉ ተገቢ አይደለም በማለት ሥሕተቱ ቢታረም ተቃውሞ የሌለው መሆኑን ገልጿል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ እኛም እንዲጣራ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡የፌዴራል ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 9/2 የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ሰሚነት ሥልጣኑ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሰጠው ውሳኔ የተለየ ውሳኔ በሰጠባቸው ጉዳዮች ላይ የይግባኝ ሥልጣን እንዳለው ይደነግጋል፡፡

የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 75 (1)እና(2) በዋስትና ወረቀት ለመለቀቅ የቀረበውን ማመልከቻ ፍ/ቤቱ ያልተቀበለው እንደሆነ ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ቅሬታውን ማቅረብ እንደሚቻል እና በዚህ ጉዳይ ላይ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ይግባኝ የሌለው መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ሆኖም በድንጋጌው ርዕስ ላይ እንደተገለጸው የዚህ ድንጋጌ ተፈጻሚነት ተከሳሹ በዋስትና ወረቀት እንዲለቀቅ ጠይቆ ባልተፈቀደ ጊዜ እንጂ የሥር ፍ/ቤት የተከሳሽን የዋስትና መብት ጠብቆ ዓቃቤሕግ ባቀረበው ይግባኝ መነሻነት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤት የተከሳሽን የዋስትና መብት በመጠበቅ የሰጠውን ውሳኔ በመሻር በሰጠው ውሳኔ ላይ ተከሳሽ ይግባኝ እንዳያቀርብ ተፈጻሚ የሚሆን አይደለም፡፡ በወንጀል ሥነ ስርዓት ሕጉ ቁጥር 75 (2) ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ይግባኝ

የለውም በማለት የተደነገገው ድንጋጌ ተከሳሹ በበታች ፍ/ቤት የተፈቀደለት የዋስትና መብት በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በተሻረበት ጊዜም የተከሳሹ ይግባኝ የማቅረብ መብት እንደሚከለክል አድርጎ መተርጎም የዜጎችን ይግባኝ የማቅረብ መሠረታዊ መብት የማጣበብ ውጤት ያለው ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካችን የዋስትና መብት የሻረው ተጠሪ ባቀረበው ይግባኝ መነሻነት በመሆኑ አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 9/2 መሠረት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩን በዚህ አግባብ በማየት መወሰን ሲገባው የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 75/2 ሁለተኛ ይግባኝ አይፈቅድም በማለት የሰጠው ውሳኔ በሕገመንግሥቱ ዕውቅና ያገኘውን የአመልካችን ይግባኝ የማለት መብት ያጣበበ እና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 144037 ሐምሌ 28 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195/2/ለ/2 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 194317 ሠኔ 05 ቀን 2009 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ላይ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው ብለናል፡፡
3. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች ድጋሚ ይግባኝ የማቅረብ መብት የለውም በማለት የሰጠው ውሳኔ የተሻረ መሆኑን አውቆ አመልካች ያቀረበውን ይግባኝ መርምሮ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡

**-መዝገበ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጌ